የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9[th] Year No. 47
ADDIS ABABA– 8[th] April, 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፯/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ማቋቋሚያ
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፩፻፵፭

CONTENTS

Proclamation No. 327/2003
Establishment of the National Reserve Force
Proclamation .......................................... Page 2145

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፯/፲፱፻፺፭
## የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የሕዝቡ ሉዓላዊነትና ሕገ–መንግሥታዊ ሥርዓቱ አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ የመከላከያ ሠራዊቱ አካል በመሆን የሚመክትና የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ፈጥኖ ለሕዝቡ ሊደርስ የሚችል፤ በሰላም ጊዜ መደበኛና የግል ሥራውን የሚያከናውን ሕዝባዊ መሠረት ያለው ብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፯) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፯/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ
የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

## PROCLAMATION NO. 327/2003
## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF NATIONAL RESERVE FORCE

WHEREAS, it is found necessary to organize a Reserve Force with strong mass basis which safeguard the peoples' sovereignty, operates together with the Defense Forces when the constitutional order is endangered, natural catastrophe occurred and carry out its normal private activities in time of peace.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (7) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the ''Establishment of the National Reserve Force Proclamation No. 327/2003.

2. *Definitions*
In this Proclamation unless the context otherwise requires:

፩) "የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል አገልግሎት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤
፪) "የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል አባል" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ተመዝግቦና አስፈላጊውን ሥልጠና ወስዶ አገልግሎት ለመስጠት የሚጠባበቅ ሰው ነው፤
፫) "አዛዥ" ማለት በአገር መከላከያ ሠራዊት ወይም በብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል በማናቸውም የዕዝ ጠገግ ላይ የሚገኝ የሠራዊት ክፍልን ለማደራጀት፣ ለማስተዳደር እና ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤
፬) "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የአገር መከላከያ "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ነው፣
፭) "ምልምል" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ውስጥ ለማገልገል የተመለመለ ማንኛውም ሰው ነው፤
፮) "የአገር መከላከያ ሠራዊት" ማለት የምድር ኃይል እና የአየር ኃይል ነው፣
፯) "የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ማደራጃና ማስተባበሪያ ቢሮ" ማለት በአገር መከላከያ ሚኒስቴር ሥር ተቋቁሞ የሚገኝ የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይልን በበላይነት የሚያደራጅ፣ የሚያስተዳድርና የሚመራ ነው፣

## ክፍል ሁለት
## መሠረታዊ ድንጋጌዎች

፫· መቋቋም
፩) የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ከዚህ በኋላ "ተጠባባቂ ኃይል" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣
፪) ተጠባባቂ ኃይሉ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል

፬· ዓላማ
የተጠባባቂ ኃይል ዓላማ
፩) የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከማንኛውም አደጋ በአስተማማኝ ለመጠበቅ፣
፪) በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊትን ተቀላቅሎ ለመሠማራት፣
፫) ሰው ሠራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ሲከሰቱ ፈጥኖ በቦታው ላይ በመገኘት ዕገዛ ወይም እርዳታ ለመስጠት።

፭· ስለተጠባባቂ ኃይል አደረጃጀት
፩) በአገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚመራ የተጠባባቂ ኃይል በሁሉም የፌዴራሉ መንግሥት ክልሎች ይደራጃል፣
፪) የተጠባባቂ ኃይሉን የሚያደራጅና የሚያስተባብር ቢሮ በመከላከያ ሚኒስቴር ሥር ይደራጃል፤
፫) ቢሮው በክልሎች ሥራውን የሚመሩና የሚያስተባብሩ የላይዘን ጽሕፈት ቤቶች ይኖሩታል። የላይዘን ጽሕፈት ቤቶች ሥራቸውን ከክልል መስተዳድር ጋር ተቀናጅተው ይመራሉ፤
፬) የተጠባባቂ ኃይሉ በወረዳ ደረጃ በአሃድ ተዋቅሮ እንዲደራጅ ይደረጋል።
፭) እንደ አስፈላጊነቱ ቢሮው በመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግሥትና የግል ተቋማት ሕዝባዊ ማኅበር ውስጥ ተግባሩን መፈፀም የሚያስችለው የላይዘን ጽሕፈት ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

፮· ምዝገባና ምልመላ
የተጠባባቂ ኃይሉ ቢሮ በሚያወጣው የምዝገባና የምልመላ መስፈርት መሠረት የፌዴራል መንግሥት ክልሎች የተጠባባቂ ኃይልን ምዝገባ ያካሂዳሉ፣

፯· የምልመላ መስፈርት
የምልመላ መስፈርት በደንብ ይወሰናል።

፰· የምዝገባ መታወቂያ ወረቀት
በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት ለተጠባባቂ ኃይሉ የተመለመለ ፣ የሠለጠነ እና ተቀባይነት ያገኘ ሰው መታወቂያ ደብተር ይሰጠዋል።

1) "National Reserve Force Service" means a service to be rendered pursuant to Article 12 of this Proclamation.
2) "National Reserve Force Member" means any person registered and take the necessary training to render service in accordance with this Proclamation.
3) "Commander" means a person authorized to direct, and lead administer a military unit formed in any level of the National Defence or National Reserve Force.
4) "Minister" or "Ministry" means the Minister or the Ministry of National Defense respectively.
5) "Inductee" means any person who is inducted in the national reserve force in accordance with this Proclamation.
6) "National Defense Force" means the Ground Force and the Air Force.
7) "National Reserve Force Organization and Coordination Buraeu" means a Bureau established under the Ministry of National Defence which coordinates and administer as superior authority the work of the National Reserve Force.

## PART TWO
## BASIC PROVISIONS

3. *Establishment*
1) There is hereby established the National Reserve Force, hereinafter called the "Reserve Force"
2) The Reserve Force is accountable to the Minister.

4. *Objectives*
Objective of the Reserve Force
1) To safeguard the country's sovereignty and to protect vigilantly the constitutional order.
2) to be deployed together with the National Defence Force at times of war and state of emergency.
3) To reach promptly at any sight and assist wherever human or natural disaster occurs.

5. *Organization of the Reserve Force*
1) Reserve Force shall be organized in all states of the Federation under the leadership of the Ministry.
2) A Bureau will be established to organize and coordinate the Reserve Force under the Ministry.
3) Liason Offices which lead and coordinate the required activities will be established at Regional level by the Bureau. The Liason Offices perform their work in collaboration with the Regional Administration.
4) The lowest level of the Reserve Force shall be organized at the Woreda Administration.
5) The Bureau may establish Liason Office to perform its functions in government offices, private or government institutions or public associations.

6. *Registration and Inductment*
*States of the Federation shall register the Reserve Force in accordance with the criteria to be issued by the Bureau.*

7. *Criteria for Inductment*
criteria for inductement shall be determined by Regulations.

8. *Certificate of Registration*
Any person registered persuant to Article 7 of the Proclamation shall be issued with a certificate of registration.

## ክፍል ሦስት
## የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል አገልግሎት ሁኔታዎች

**፱. ወታደራዊ ሥልጠና**

፩) ተመልማዮች መሠረታዊ ወታደራዊ ሥልጠና ወደሚያገኙበት ማሠልጠኛ ማዕከል ይገባሉ፤

፪) ተጠባባቂ ኃይሉ ለተልዕኮው የሚያበቃው መሠረታዊ ወታደራዊ ሥልጠና ይሰጠዋል፤

፫) በሥልጠና ወቅት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መጠለያ፣ ምግብ፣ አልባሳት፣ የኪስ ገንዘብ፣ ሕክምና፣ የትምህርት መርጃ ዕቃዎች በነፃ ያገኛል፤

፬) ወታደራዊ ሥልጠናውን ያጠናቀቀ ምልምል የምሥክር ወረቀት ይሰጠዋል።

፭) ወታደራዊ ሥልጠናው እንደተጠናቀቀ የተጠባባቂ ኃይል አባሉ ወደየመጣበት አካባቢ እንዲመለስ ይደረጋል፤

፮) ወደመጣበት ከተመለሰ በኋላ በየዓመቱ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር የማጠናከሪያ ሥልጠናና ልምምድ ሊሰጠው ይችላል።

**፲. ክ ተ ት**

፩) ማንኛውም የተጠባባቂ ኃይል ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ሚኒስትሩ በሚወስነው ቦታና ጊዜ የመገኘት ግዴታ አለበት፤

፪) ጥሪው የሥልጠና፣ የልምምድ ወይም የክተት ሊሆን ይችላል።

**፲፩. ስለ ምደባ**

ወታደራዊ ሥልጠናውን ያጠናቀቀ የተጠባባቂ ኃይል አባል ለአገልግሎት በሚፈለግበት ጊዜ በምድር ኃይል ወይም በአየር ኃይል ውስጥ ተመድቦ ያገለግላል።

**፲፪. የአገልግሎት ዘመን**

፩) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ የተጠቀሰው ወታደራዊ ሥልጠና ያጠናቀቀ የተጠባባቂ ኃይል አባል (መደበኛ የውትድርና አገልግሎት እንዲሰጥ በሚፈለግበት ጊዜ) ለ፯ (ሰባት) ዓመት ያገለግላል። ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረትም ውል ይፈጽማል፤

፪) ለተጨማሪ አገልግሎት በጋራ ስምምነት ሊራዘም የሚችል ሲሆን ሆኖም አገልግሎቱ ከ፴፰ ዓመት ዕድሜ ሊያልፍ አይችልም፤

፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የአገልግሎት ዘመን በክተትና በጦርነት ጊዜ ሊራዘም ይችላል።

**፲፫. ስለሜዳይና ሽልማት**

፩) ማንኛውም የተጠባባቂ ኃይል አባል በአገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ሆኖ ለሰጠው አገልግሎትና ለፈጸመው ጀግንነት በአገር መከላከያ ሠራዊት አዋጅ መሠረት ሜዳይ ወይም ሽልማት እንዲያገኝ ይደረጋል፤

፪) አንድ የተጠባባቂ ኃይል አባል አገልግሎቱን ጨርሶ በክብር ሲሰናበት የተጠባባቂ ኃይል ሜዳይና የምሥክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

፫) በራሱ ፈቃድ ሳይሆን በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎቱን ቢያቋርጥ ያቋረጠበት ምክንያት ተጠንቶ የምስክር ወረቀት ሊሰጠው ይችላል።

**፲፬. ወታደራዊ ሕጎችን፣ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን ስለማክበር**

ማንኛውም የተጠባባቂ ኃይል አባል በሚሠለጥንበትና ውትድርና አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ወታደራዊ ሕጎችን፣ መመሪያዎችንና ትእዛዞችን ማክበር አለበት።

## *PART THREE*
## *CONDITIONS OF SERVICE OF RESERVE FORCE*

9. *Military Training*

1) Inductees shall be admitted into training centres to acquire basic military training.
2) The Reserve Force shall get basic military training which enables him to accomplish his mission.
3) Any inductee is entitled in accordance with the directives of the Ministry to rations, lodging, clothing, pocket-money, medical care and teaching aids.
4) Certificate shall be issued after completion of military training.
5) After completion of military training, the inductee shall be returned back to their home.
6) Training and practice together with the Defense Forces may be given after members of the Reserve Force return home.

10. *Mobilization*

1) Any member of the Reserve Force when called upon shall made himself available at such place and time as shall be determined by the Ministry.
2) The call up may be for training, exercise or mobilization.

11. *Assignment*

Any member of the Reserve Force after completion of military training and needed to render service shall be assigned in the Ground Force or in the Air Force.

12. *Term of Service*

1) Any member of the Reserve Force who has completed the military trainng pursuant to Article 9 of this Proclamation shall serve for 7 years and sign contract of employment in accordance with the directives issued by the Ministry.
2) For additional service, the period may be extended by mutual consent without, however, going beyond the age of 38.
3) Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article the term of service shall be extended during mobilization and in times of war.

13. *Medals and Prizes*

1) Any member of the Reserve Force shall be awarded with medals or prizes for notable service, heroism in accordance with the Proclamation of the Defense Forces.
2) Upon completion of term of service as member of the Reserve Force, he shall be entitled to medal of the Reserve Force and certificate.
3) Where the service of a member of the Reserve Force is terminated not voluntarily but for various other reasons before completion of the required term of service, he shall be given certificate by ascertaining the reasons of the termination.

14. *Observance of Military Laws, Directives and Orders*

Any member of the Reserve Force shall observe military laws, directives and orders while on training and active service.

፲፭· <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

ማንኛውም የተጠባባቂ ኃይል አባል በሥልጠናም ሆነ መበደኛ ወታደራዊ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ለሚደር ስበት የአስተዳደር በደል በሠራዊቱ የዲስፕሊን መመሪያ መሠረት አቤቱታ የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት መብት አለው።

## ክፍል አራት
## ስለ አገልግሎት ፣ ማዕረግና ስንብት

፲፮· <u>ስለ አገልግሎት</u>

፩) አገልግሎቱን በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ በየትኛውም ክፍልና ቦታ ተመድቦ እንደሠራዊቱ ይፈጽማል

፪) በመደበኛ ውትድርና አገልግሎት ላይ የሚገኝ ማናቸውም የተጠባባቂ ኃይል አባል እንደማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ቀለብ፣ ልብስ ፣ መጓጓዣ፣ ቤት፣ ሕክምና እና የማዕረጉን ደመወዝ ያገኛል።

፲፯· <u>ስለ ማዕረግ</u>

፩) ማንኛውም የተጠባባቂ ኃይል አባል ከሠራዊቱ ጋር ተቀላቅሎ አገልግሎት ሲሰጥ የሥራ ብቃቱ፣ ሥነ ሥርዓት አክባሪነቱ እና የሥራ አፈጻጸሙ እየተገመገመ በመከ ላከያ ሠራዊት የማዕረግ ዕድገት መመሪያ መሠረት የማዕረግ ዕድገት የማግኘት መብት አለው።

፪) በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ለዕዝና ቁጥጥር የሚያስፈልጉ የኃላፊነት ደረጃዎች እየተጠኑ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ማዕረጎች ሊሰጡ ይችላሉ።

፲፰· <u>አገልግሎት ስለሚቋረጥበት ምክንያት</u>

ማንኛውም የተጠባባቂ ኃይል አባል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ምክንያቶች ሲያጋጥሙ አገልግሎቱን አቋርጦ እንዲሰናበት ይደረጋል፤

፩) የቅጥር ውሉ ዘመን ሲያልቅ፣

፪) በዕድሜ ምክንያት አገልግሎት መስጠት የማይችል ሲሆን፣

፫) የአእምሮ መታወክ ወይም የአካል ጉዳት ደርሶበት ለአገልግሎት ብቁ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፣

፬) በወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘና ጥፋቱም ለሥራው ብቁ አያደርገውም ተብሎ ሲወሰን።

፲፱· <u>ስለ ካሣ</u>

የተጠባባቂ ኃይል አባል በሥልጠና ወይም በአገልግሎት ላይ እያለ ጉዳት ቢደርስበት ለመደበኛ ሠራዊት የሚከፈለው ካሣ (ድጐማ) በሠራዊቱ መመሪያ መሠረት ያገኛል፤ የሞት አደጋም ከጋጠመው በጡረታ ሕግ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል አምስት
## የተጠባባቂ ኃይል ቢሮ ኃላፊ
## ሥልጣንና ተግባር

፳· <u>የተጠባባቂ ኃይል ቢሮ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩) ለተጠባባቂ ኃይል አባልነት የሚያበቁ የምልመላ መስፈ ርቶችን ያወጣል፤

፪) ስለተጠባባቂ ኃይል ሥልጠና፣ ትጥቅ፣ ጥቅማጥቅም፣ ስለዲስፕሊን እርምጃና ጠቅላላ አስተዳደር አስፈላጊውን መመሪያ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በተግባር ላይ ያውላል፤

፫) ተጠባባቂ ኃይሉ ስለሚከትበት፣ ስለሚሰማራበት፣ ስለግዳጅ አፈፃፀሙና ስለስንብቱ መመሪያ ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬) ይህ አዋጅ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

፭) ከሚኒስትሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

15. *Complaints*

Any member of the Reserve Force, whether on training or military service, shall have the right to complain against any administrative wrongs and obtain decision in accordance with the Defence Forces desciplinary directives.

## PART FOUR
## SERVICE, PROMOTION AND TERMINATION OF SERVICE

16. *Service*

1) Any member of the Reserve Force shall render service in any place and in any unit of the Defense Forces.
2) Any member of the Rerserve Force while on active service shall be entitled as member of the Defense Forces to rations, uniform, transportation, lodging, medical care free of charge and salary.

17. *Ranks*

1) In accordance with directives on promotions to be issued by the Ministry any member of the Reserve Force shall be promoted for excellence in the performance of duties and observance of discipline while rendering service in the Defense Forces.
2) In accordance with the directives of the Ministry ranks may be given for command and control positions at Woreda and Kebele levels.

18. *Termination of Service*

The service of a member of the Reserve Force shall be terminated upon:

1) Expiry of his contract of employment,
2) can't render service due to age limitation,
3) Unfitness for military service owing to serious illness or mental or physical handicap.
4) Being criminally convicted by law court and where decided that the offence disqualified him from service.

19. *Compensation*

A member of the Reserve Force shall be entitled to compensation like that of the defense forces for injuries sustained while rendering service or on training, and in case of death it shall be handled in accordance with the pension Law.

## PART FIVE
## POWERS AND DUTIES OF THE HEAD OF THE RESERVE FORCE BUREAU

20. Powers and Duties of the Head of the Reserve force Bureau

1) Prescribe the criteria for membership of the Reserve Force.
2) Prepare direcives for training, armament, incentives, disciplinary measures, general service and implement upon approval.
3) Prepare directives for mobilization, deployment, combat performance and termination and implement upon approval.
4) Follow up implementation of the National Reserve Force Proclamation.
5) Perform other functions assigned to him by the Minister.

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፩· የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የግል ድርጅት ይህን አዋጅ ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት።

**፳፪· የወታደራዊ ሕጐችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት**

፩) በበዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ውትድርና አገልግሎት የሚሰጥ የተተጠባባቂ ኃይል አባል የሚፈጽመው ወታደር ነክ ወንጀል በወታደራዊ ፍርድ ቤት ይታያል ፤

፪) ማንኛውም የተጠባባቂ ኃይል አባል የሥነ ሥርዓት ጉድለት በፈጸመ ጊዜ በሀገር መከላከያ የዲስፕሊን መመሪያ መሠረት ጉዳዩ እንዲታይ ይደረጋል ።

**፳፫· የተሻሩ ሕጐች**

የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል ፤

፩) የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፪/፲፱፻፷፭

፪) የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፬/፲፱፻፷፮

፫) የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፰/፲፱፻፸፭

**፳፬· ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ማውጣት ይችላል ።

**፳፭· መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያ ዎችን ያወጣል ።

**፳፮· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

## *PART SIX*
## *MISCELLANEOUS PROVISIONS*

*21. Duty to Cooperate*

Any person, government office or private organization has the duty to cooperate in the implementation of this Proclamation.

*22. Applicability of Military Laws and Directives*

1) Any member of the Reserve Force rendering military service in accordance with Article 12 of this Proclamation when committing military offence shall be tried in military courts.

2) Any member of the Reserve Force violating disciplinary matters, will be tried in accordance with the disiplinary directives of the Ministry.

23. Repeal

The following are hereby repealed.

1) The National Military Service Proclamation No. 322/1973.

2) The National Military Service Regulation No. 444/1973.

3) Establishment of National Military Service Proclamation 238/1983.

24. Power to Issue Regulations

The Council of Ministers shall have the power to issue regulations necessary for the implementation of the Proclamation.

*25. Power to Issue Directives*

The Ministry shall have the power to issue directives necessary for the implementation of this Proclamation.

26. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of 8th day of April, 2003.

Done at Addis Ababa, this 8th day of April,2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE